የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፪
አዲስ አበባ ጥር ፳፬ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 12
ADDIS ABABA 1st February 2011

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፺፮/፳፻፫

የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………ገፅ ፭ሺ፮፻፺፭

## CONTENTS

**Regulation No. 196/2010**

Ethiopian Conformity Assessment Enterprise Establishment
Council of Ministers Regulation…… ……………. Page 5695

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፺፮/፳፻፫

## የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፺፮/፳፻፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. <u>መቋቋም</u>

፩/ የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

፫. <u>ተቆጣጣሪ ባለስልጣን</u>

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 196/2010

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN CONFORMITY ASSESSMENT ENTERPRISE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. <u>Short Title</u>

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Conformity Assessment Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 196/2010".

2. <u>Establishment</u>

1/ The Ethiopian Conformity Assessment Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. <u>Supervising Authority</u>

The Ministry of Science and Technology shall be the supervising authority of the Enterprise.

4. <u>Head Office</u>

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as necessary.

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

ዓላማ

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች ብቃት ያለው የሰርተፊኬሽን፣ የኢንስፔክሽንና የላቦራቶር ፍተሻ አገልግሎቶችን በማደራጀት፡-

፩/ አምራች ድርጅቶች ወይም አገልግሎት ሰጪዎች አግባብነት ያላቸውን ብሔራዊ ወይም ዓለም ዓቀፍ ደረጃዎችንና ሕጋዊ መስፈርቶችን ማሟላታቸውን በመመርመር የተስማሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት፤

፪/ የሀገሪቱ የወጪ ምርቶች የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ወይም ዓለም ዓቀፍ ወይም የሌሎች ሀገሮች ደረጃዎችንና ሕጋዊ መሥፈርቶችን ማሟላታቸውን በመመርመር የተስማሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት፤

፫/ ከውጭ የሚገቡ ምርቶች አግባብነት ያላቸውን ብሔራዊ ወይም ዓለም አቀፍ ደረጃዎችንና ሕጋዊ መሥፈርቶችን ያሟሉ መሆኑን በመመርመር የተስማሚነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመስጠት፤

፬/ የሚሰጠው የላቦራቶር ፍተሻ አገልግሎት ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ከሌሎች ብሄራዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም ዓቀፍ የላቦራቶር ፍተሻ ተቋማት ጋር የፍተሻ ውጤትን የርስ በርስ ንፅፅር በማድረግ የማረጋገጥ ፕሮግራም ላይ የመሳተፍ፤

፭/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፭፻፵፫ ሚሊዮን (አምስት መቶ አርባ ሦስት ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህም ውስጥ ብር ፩፻፴፭ ሚሊዮን ፮፻፵፮ሺ፯፻፴፫ ከ፶፫ ሣንቲም (አንድ መቶ ሠላሳ አምስት ሚሊዮን ስድስት መቶ አርባ ስድስት ሺ ሰባት መቶ ሠላሣ ሦስት ብር ከሃምሳ ሦስት ሣንቲም) በጥሬ ገንዘብና በአይነት ተከፍሏል፡፡

ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በእዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጥር ፳፬ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

5. **Purposes**

The purposes for which the Enterprise is established are, by organizing robust certification, inspection and testing laboratory services, to:

1/ provide certificate of conformity to production enterprises or service providers by assessing the conformity of their production processes or service provisions to the relevant national or international standards and legal requirements;

2/ provide certificate of conformity with respect to the country's export products by assessing their conformity to the relevant Ethiopian standards, international standards or the standards of other countries;

3/ provide certificate of conformity with respect to imported products by assessing their conformity to the relevant national or international standards and legal requirements;

4/ participate in inter-laboratory comparisons and proficiency test scheme between various regional and international testing laboratory institutions with a view to proving the proficiency of its testing laboratory services;

5/ carry out other related activities necessary for the attainment of its purposes.

6. **Capital**

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 543,000,000 (five hundred forty three million Birr) of which Birr 135,646,733.53 (one hundred thirty five million six hundred forty six thousand seven hundred thirty three Birr and fifty three cents) is paid up in cash and in kind.

7. **Liability**

The Enterprise shall not be held liable beyond its total assets.

8. **Duration of the Enterprise**

The Enterprise is established for an indefinite period.

9. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 1st day of February, 2011.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት